----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

# ዓለም አቀፍ ቅንጅት በዓለም ዙርያ እንዲደረግ የጠራው የሻማ ማብራትና የጸሎት ሥነ-ሥርዓት በስዊዘርላንድ ለየት ባለ መልኩ ታሰቦ ዋለ!

**ዙሪክ** 23. 6. 1999

በብዙሃኑ ኢትዮጵያውያን አመኔታን አትርፈው የተመረጡት የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ መሪዎች፣ የነጻ ው ፕሬስ አባላት፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችና ባጠቃላይ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ካለምንም ቅድመ ሆኔታ አሁኑኑ ይፈቱ! ፍርድ ዘገዬ ማለት ፍርድ ተነፈገ ማለት ነው በሚል መሪህ ጥሪ ስር የተዘጋጀው የሻማ ማብራትና የጸሎት ፕሮግራም በተሳካ ሁኔታ ተደረገ። የወያኔው የማዘናጋትና የማዘግየት ሸር መቀጠል የለበትም የሚል መን ፈስ ያለው በራሪ ወረቀት ለሕዘብ ተበትኗል። በተለይ በዙሪክ በበርንና በቢል ከተማዎች ተመሳሳይ መልእክቶች የተላለፉ ሲሆን የዙሪኩን ከሁሉም ለየት ያደረገውና የአላፊ አግዳሚውን ቀልብ የሳበ የተቃውሞ አይነት መታየ ቱ ነበር።

መሪዎቻችንና የሕዝብ ወገን የሆኑት የነጻው ፕሬስ አባላት በግፍ ከታገቱ 486 ቀናት ተቆጥረዋል። የፓርላማ ስርዓ ት በኢትዮጵያ እንዲሰርጽ ምርጫ 97 በር ከፈተ ሲባል በፍርደ ገምድሎች ተሰናክሏል፣ የሕዝብ ድምጽ አይሰ ረቅ፣ ሕገ መንግሥቱ የሚፈቅደው ተቃውሞን መግለጽ መከልከል የለበትም በማለታቸው በ «ዘር ማጥፋትና ክህ ደት»ተወንጅለው መከራ በማየት ላይ ያሉበትን ሁኔታ ለማሳየት ከሰልፈኞቹ አንዱ አቶ ዘ.ጌ.(ምስሉን ይመልከቱ) በኢትዮጵያ ስም ለኢትዮጵያ መታሰራቸውን ለማሳየት በአረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለማት ባሉት ማሰርያ እጆቹን አስሮ፣ በቀዝቃዛ ሲሚንቶ ላይ እንዲተኙና እንዲቀመጡ መደረጋቸውን ለማሳየት በሚያንሰፈስፍ ቀዝቃዛ የአየር ጸባይና እጅግ በቀዘቀዘ አስፋልት ላይ በመተኛትና በመቀመጥ ተቃውሞውን ሁሉም ሊረዳው በሚችለው መንገድ ገልጿል።

ይኽንን ያልተለመደ ትንግርት ለምን እንደዚህ እንደሆነ ያልጠየቀ ተላላፊ አልነበረምናምክንያቱ በአጥጋቢ ሁኔታ ተገልጾ፤ የተዘጋጁት በራሪ ወረቀቶች ተበትነው ተጨመሪ መረጃ ሆነዋል።የዙሪኩ ፕሮግራም የተካሄደበት «ባህን ሆፍ ሽትራሴ -ፓራደፕላትዝ» የስዊ ባንኮች .የማእከላዊው (ሴንትራል) ባንክም ጭምር ዋና መስሪያ ቤቶች ያሉበ ት አካባቢ በመሆኑ የሚዘወተረው በከበርቴዎች፤ እንዱስትሪያሊስቶችና በኤኮኖሚውና በፖለቲካው መስክ አንቱ የተባሉ ግለሰቦች የእኛን ጣጣ እንዲያዩና እንዲያነቡ ተገደዋል።

በበርንና በቢል የተካሄዱትም የሻማ ማብራት ፕሮግራሞች በተሳካ ሁኔታ ተከናውነዋል። በስዊዘርላንድ የቅን ጅት የድጋፍ ድርጅት የታሰሩት እስኪፈቱ መፈታታቸውን ከሚጠይቁ ጋር አብሮ በመቆም፤ በሀገራችን ሰላም ሰ ፍኖ የሕግ የበላይነት እስኪረጋገጥና የሕዝብ ድምጽ ተከብሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመረጣቸው መተዳደር እስኪጀ ምር ድረስ ትግሉን ይቀጥላል።

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ!


Postfach 1124 8152 Opfikon Schweiz

E-Mail: kinjitch@yahoo.com and kinjit.cudp@bluewin.ch , www.kinijitswiss.org